**ህወሃት የትግራይ ጠላት ወይስ ነጻ አውጭ?**

**በአዲስ ተስፋ**

ብዙዎቻችን እንድምናውቀው ህውሃት ኢትዮጵያን የማፍረስ አጀንዳ ይዞ ለመጀመሪያ ሲነሳ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ 1968 ዓም በጻፈው ማኒፌስቶው የትግራይ ጠላት ዐማራ መሆኑን ያለምንም ይሉኝታ አስቀምጦታል። በተለያየ ጊዜ ለመሪዎቹ ይህ ጥያቄ ሲነሳላቸው ለመካድ ቢሞክሩም መኜና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም እንደሚባለው እድሜ ለቴክኖሎጅና በኮምፒዩተሮቻችን እናገኘዋለን። ዐማራ ዋና ጠላት ተደርጎ ሲፈረጅ ዛሬ ሁሉም የማይክደው ግቡ ግን በዐማራ ላይ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ስትራቴጂካዊ እቅድ ነበረ። እጅግ ብዙ ማስረጃዎች የሚቀርብበት የህወሃት ጸረ ዐማራነት ለዘመናት ከቀረው ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከዐማራውም የተሰወረና ስልታዊ ነበር። አቶ በረከት ስምዖን ለዐመታት ታገልሁለት የሚሉትን ይህንን ህዝብ ዛሬ  ዘረኛ እንደሆነ ሊነግሩን ሲሞክሩ መደበቂያቸው ህወሃት የሆነበት ምስጢር ከተራ አሉባልታ ይልቅ በተግባር የዚያ ኢትዮጵያን የማፍረስ ስውር ተጠሪ እንደነበሩ በመቀሌው ጥናታዊ ጽሁፋቸው አሳይተውናል። የህወሃት መሪዎችና የስውሩ ተልዕኮ አራማጆች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መድረኩን ሲያገኙ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች በማለት ለምን እንደሚጀምሩ በዙዎቻችን ላይገለጥልን ይችላል። ይህ ካልሆነ ወይም ያ ካልሆነ ኢትዮጵያ  ትፈርሳለች በማለት ያለመጠራጠር አፋቸውን ይከፍታሉ። በነገራችን ላይ ይህ ቃል የሚነገረው ባጋጣሚ አይደለም። ደግሞም ህወሃቶችና መሪዎቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ለዚህ አላማ ምልምል ወይም አጋር የሆኑ ሁሉ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ነጠላ ዜማቸው ነው።ህገ መንግስቱ የማይከበር ከሆነ ሀገር አይኖረንም፤ ኢትዮጵያም ትፈርሳለች ብለው በአደባባይ ከተናገሩት መካከል አባይ ጸሃየ፣ ስብሃት ነጋ፣ ስዩም መስፍን ፣ በረከት ስምዖን፣ ደብረጽዮን ገብረመድን፣ጅዋር መሃመድ፣ዳውድ ኢብሳ፣ ከበደ ጫኔ፣ ህዝቂል ጋዲሳ፣ የህወሃት ካድሪዎችና አክራሪ አነጋውያን ይገኙበታል። አሁን ሊገባን የሚገባው በእርግጥም ይህ ስርዓት ከፈረሰ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ አድራሻቸው የት እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው።የሆነስ ሆነና ዐማራን ጠላት ኢትዮጵያን ደግሞ ማፍረስ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ይህ ቡድን በእርግጥ የትግራይ ነጻ አውጪ ነበርን? በጥሞና ስንመለከተውስ ለትግራይ ሃይነትና ልእልና ታግሏልን?ከሰሞኑ በተካሄደውና የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው ውይይት ላይ የህዝብ ለህዝብ ማቀራረብ ዓላማው ሊደገፍ የሚገባው ቢሆንም አንዳንድ ምሁራን ተብለው ንግ ግር እንዲያደርጉ መድረኩ ከፈቀደላቸው የምሁራን ማሃይሞች የተሰማው ጭፍን የካድሪ አይሉት ሰላም ፈላጊ ጩኸት አስተዛዛቢ ነበር። በርግጥ ከልባቸው ስለሰላም የሚያስቡና ፖለቲከኞችን የገሰጹ ፕሮፌሰሮችም ነበሩ። አንደኛዋ ምሁር ነኝ ባይ ለሰላም እየሰራ ያለው ህወሃት ብቻ ነው ብላናለች። ይህችው ደንቆሮ ምሁር ነኝ ባይ የህወሃትን ለሰላም በርትቶ መስራት ብቻ ሳይሆን ከመቼውም ጊዜ በላይ መጠንከሩንና በህዝቡ ውስጥ መኖሩን ልታስረዳን ሞክራለች። በትክክክል የፕሮፌሰር ተኮላ ሃጎስ ደቀመዝሙር እንደሆነችና ለህዝቧ ሳይሆን ለሆዷ እንደምትኖር ሌላ ማረጋገጫ አያስፈልግም። ጌታቸው ረዳ እንዳለው ሁሉም የትግራይ አክቲቪስቶች ድንቆሮዎች ናቸው ማለት አልፈልግም ፤ ነገር ግን ህወሃት የዐማራ ጠላት የኢትዮጵያም አፍራሽ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ህዝብ ዋና ጠላት መሆኑን ያልተረዱ በርካቶች ናቸው።ከወራት በፊት ስለ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ጽፌ ነበር፤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም ከ አንዴም ሁለቴ የክልሉን ካርታ ከጋምቤላና ከትግራይ ጋር እንደሚዋሰን በማብራሪያ ካስረዳ በኋላ በስ ህተት ነው በማለት ይቅርታ ጠይቆ ነበር። የዋሃን ሁላችንም ይቅርታውን ተቀብለን አልፈነዋል። የመረረውን  እውነት አቶ ያረጋል አይሸሹም ለ አስራ አምስት አመታት ቤንሻንጉልን የመሩት ትናንት ከፋና ቴለቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ አረጋገጡልን። ቤንሻንጉል አሉን አቶ ያረጋል በንሻንጉል በቻርተሩ መሰረት በሰሜን ወልቃይት ድረስ በደቡብ ደግሞ ጋምቤላ ድረስ መሆኑን አስረዱን። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የትግራይ አክቲቪስቶች ለምን ወያኔን የመቃውም አቅም አይኖራቸውም በማለት እንደነቃለን። ወያኔን የ አምላክ ያህል እንዴት እንደሚያመልኩም አይገባንም ነበር። በአንጻሩ ደግሞ የትግራይ ህዝብ በሌላው እንደተገፋ እንዲሰማው ሆን ተብሎ የሚሰራው ፕሮፓጋንዳም ግልጽ አይሆንልንም፣በፍጹም ኢትዮጵያዊነታቸው ጽኑ የሆኑ የትግራይ ተውላጆች እየታደኑ እንደተገደሉ የቀሩት ደግሞ በእስር እንዲማቅቁ የሆነበት ምክን ያትም የተሰወረ ነው። ሌላው አስገራሚውና በጥልቀት የማንመረምረው ደግሞ ወያኔን እቃወማለሁ የሚሉትና አሁን የትግራይ ህዝብ አማራጭ ፓርቲ ነን ብለው የሚንቀሳቀሱት እነዶክተር አረጋዊ በርሄን የመሳሰሉ ጉምቱ የፖለቲካ ሰዎች ተሳስተው እንኳ ህወሃት የ አማራ ጠላት ሆኖ ነው የተነሳው ሊሉን አይፈልጉም።የወያኔን ኢትዮጵያን አፍራሽነትም አይናገሩም፣ ለራሱ ስልጣን ማራዘሚያ ሃገሪቱን በዘር ከፋፍሎ ያዛት በማላት እንድናምናቸው ይፈልጋሉ። የህወሃትን አላማ ሰምና ወርቁን ግን በትክክል ያዉቁታል። አንድ ጥያቄ ልጠይቅና ለጊዜው ይህንን ሃሳብ በይደር አቆይቼ ወደ ሌላ ሃሳብ ለመዝለል እሞክራለሁ።**ጥያቄ** ; **ለመሆኑ የትግራይ ምሁራንና አክቲቪስቶች በአጠቃላይም  ከህወሃት ውጭ የሆነ ኤሊት እንዴት ወያኔን መቃወም አቃተው? ተራውን የትግራይን ህዝብስ ወያኔ ለምን የተገፋሁ ስሜት እንዲያድርበት በሰፊው ፕሮፓጋንዳ ይሰራበታል? አማራጭ ነን ብለው የተነሱ ተቃዋሚወችስ የወያኔን አላማ በተለይም ኢትዮጵያን አፍራሽ መሆኑን ለምን አይቀበሉም?የህዳሴው ግድብ ቀደም ብሎ የተጠናውና ምቹ የሆነው ቦታ እያለ ለምን ቤንሻንጉል ውስጥ እንዲገነባ ተፈለገ?**

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከመመለሳችን በፊት ወደ ሌላ ሃሳብ እንምጣና በመጨረሻ  ሃሳቦችን ለማያያዝ እሞክራለሁ። የወያኔ አጋር በተለይም ኢትዮጵያን ለማፍረስ አብሮ የተማማለና ጋብቻውንም እስካሁን ያላፈረሰ ኦነግ መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። ኦነግ በዚህ ጊዜ እየወሰደው ያለው እርምጃ ለብዙዎቻችን እንቆቅልሽ ነው። በተለያዩ የኦሮሞ አካባቢዎች ሰዎችን በመግደል ላይ ይገኛል። ከየዩኒቨርሲቲዎች የአማራ ተማሪዎችን እየመረጠ መግደል ብቻ ሳይሆን ለማስታረቅ የሚሞክሩ ሽማግሌዎችንም በሚዘገንን ሁኔታ እየደበደበ አያገባህም በማለት ይመልሳል። ለኦሮሞ ነጻነት ሃምሳ አመት ታገልኩ የሚል ሽማግሌ ፓርቲ ኦሮሞ ሽማግሌዎችን መደብደብ ኦሮሞ እናቶችን መግደል ሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ማሳደድ በሰፊው ተያይዞታል። **ግን ለምን ምክንያቱ ገብቶን ይሆን?**

በእርግጥ ኦሮሞ አሁን ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ በደል እየደረሰበት ይሆን? ኦነግ የኦሮሞን ህዝብ ስለሚዎድ ፍቅሩ ስላየለበት ይሆን?ዶክተር አብይ አህመድ ና አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሞን ጥቅም አሳልፈው ይሰጣሉ ብሎ የሚያስብ ካለ በእርግጥ ሞኝ ነው። ዶክተር አብይን ከጅምሩ ጀመረን በአንዳንድ ጉዳዮች የምንተቸውም ለዎጣበት ማህበረሰብ ያደላብናል ብለንም አልነበረም። ዮኦሮሞን ስነልቦናና እሴቶች ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የበታችነትም ሆነ የበላይነት ስሜት የማይሰማው ስለሆነ የተነሳበትን አላማ ከግብ እንዲያደርስ አንዳንድ እርምጃዎችን ፈጥኖ እንዲዎስድ ከመጓጓት አንጻር እንተቸው ነበር እንጂ ኦነግ ጠላት ሆኖ ይነሳበታል ብለን ግን አናስብም ነበር። ሆኖም ከወያኔ ጋር ያለውን የኦነግን ቃልኪዳል ላወቀ ይህ እንደሚሆን ማሰብ አያዳግተውም። ምክን ያቱም የኦነግና የወያኔ ስምምነት አማራን በማዳከም ኢትዮጵያን ማፍረስና አማራ በብዛት አለበት ተብሎ ከሚታሰበው ውጪ ያለውን የኢትዮጵያ ክፍል ለሁለት በመካፈል ኦሮሚያንና ታላቋን ትግራይን መመስረት ነበር።

አስገራሚው ነገር ኦነግ ዛሬ የውጊያ ሜዳ ያደረገውን የወለጋን መሬትና ከኢሉባቦር ጨምሮ በመስጠት ኦሮምያ የሚባለውን ክልል በምእራብ በኩል አብዛኛውን ለቤንሻንጉልና ጋምቤላ በመስጠት በአንጻሩ ሶማሊያን እስከ ጎዴ ድረስ በኦሮምያ የማካተት ስምምነት እንዳለ ይነገራል። ጸረ ለውጥ በመባል እዚህም እዚያም የሚነሱ ግጭቶች ባጠቃላይ ስትራቴጅካዊ የእቅድ ክንውን ናቸው። ኢትዮጵያ ስላም እንድት ሆንልንና የትም ቦታ ዜጎቻችን ተንቀሳቅሰው መኖር እንዲችሉ ምኞትና ናፍቆታችን ቢሆንም ስር የሰደደው የኦነግና የውያኔ ጋብቻ ግን ኢትዮጵያን ለማፍረስ ዝግጅት ተጠናቅቋል። ለአመታት ያክል ቅዠት እንጂ እውነት መስሎ ያልታየን የታላቂቷ ትግራይ ካርታ አሁን በትክክል የተረዳነው ይመስላል። በተለይም የቀድሞው የቤንሻንጉል ፕሬዚደንት አቶ ያረጋል አይሸሹም የቤንሻንጉልን ግዛት ከየት እስከየት እንደሆነ ትናንት ሲገልጽ እውነታውን ፍንትው አድርጎ አሳይቶናል።አቶ ያረጋል እኛ ድንበራችን በመተማ እስከ ወልቃይት መሆኑን  በምክር ቤት አጽድቀን ነበር ነገር ግን የአማራ ምክር ቤት አላጸደቀውም ሲሉ ለምን የሚል ጥያቄ ጋዜጠኛው ሲጠይቃቸው አላውቅም አሉ። በአጽንኦት መመልከት ያለብን የቤንሻንጉል ምክርቤት አጽድቅ ተብሎ እንደታዘዘና እንዳጸደቀው ነው። ለምን ቢባል አቶ ያረጋል የምክርቤቱ ሰብሳቢ ሆነው እንዲጽድቅ ሲያደርጉ ቦታውን ግን ሄደው እንዳላዩ በመጣላቸው ሪፖርት በመመስረት እንዳስጸደቁት እዚሁ ላይ ተናግረዋል።በመሰረቱ አቶ ያረጋልን በግል አውቃቸዋለሁ ፣ክፉ ሰው አይደሉም፣ ሴራውንም በደምብ የሚያዉቁት አይመስለኝም። ግዛትን ወይም ድንበርን ያህል ነገር ሳያዩ እንዲጽድቅ ማድረጋቸው ግን አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን መገልገያ እቃ ብቻ እንደነበሩ መገመት አያስቸግርም።

ታዲያ የታላቋን ትግራይን ካርታ ስናይ ጸሃፊዎችም ስለተንኮሉ ሊያስረዱን ሲሞክሩ ተረት ተረት እንጂ እውነት አይመስለንም ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን ጃዋር ሞሃመድ አምቦ ላይ መሰረቱን ያስቀመጠው የኦሮሚያ ካርታ ከትግራይ ጋር የሚዋሰን መሆኑን ልብ ይሏል። እዚህ ላይ ቢያንስ አሁን ሁሉም ሰው እንዲረዳው የሆነውን የበንሻንጉልንና የትግራይን መዋሰን የአማራ ምክርቤት አለማጽደቁ እጅግ ሊያስመሰግነው ይገባል። ምክንያቱም ብአዴን የህወሃት ቀኝ እጅ እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን በድብቅም ይሁን ይህንን ሻጥር ሳያጸድቅ መቅረቱ ተዓምር ሊባል የሚችል ነው። አሁን  ሃሳቡን ማጠቃለል ይቻላል። የሚከተሉትን አንኳር አንኳር ሃሳቦች በማንሳት ለመሰብሰብ እንሞክር።

1. ሁሉም የሚደረጉት ግጭቶች ለውጡን ለመቀልበስ ነው የሚል ታፔላ ቢሰጣቸውም በእቅድና በጥንቃቄ እየተደረጉ መሆኑን ግን መረዳት ይኖርብናል። የኦሮሚያና ሶማሊያ፣ የደቡብና ኦሮሚያ፣ የቤንሻንጉልና ኦሮሚያ እንዲሁም የአዲስ አበባ ግጭቶች ሁሉም የባለቤትነት ጥያቄን ለማንሳት ሆን ተብሎ ኦርከስትሬት የተደረጉ ናቸው። በዚህም መሰረት ኦንግ የሚያልማት ኦሮምያ ሲዳሞንና ሁለት ሶስተኛውን የሰማሊያ ክልል የሚያጠቃልል ስለሆነ እነዚህን ጥያቄዎች ወደ ፌደሬሽን ምክርቤት ለማቅረብና ለድንበር ውዝግቡ ዘለቄታዊ መፍት ሄ ለመስጠት በሚል ህጋዊ  መሰረት እንዲኖረው መሆኑ።
2. በቤንሻንጉልና በኦሮምያ መካከል ያለውም ግጭት ምእራብ ወለጋን ወደ ቤንሻንጉል ክልል በመጠቅለል  ቤንሻንጉልን ቀጥታ ከጋምቤላ ጋር ኩታ ገጠም ለማድረግ ይህም በሚመለከታቸው የህግ አካላት ህጋዊ መሰረት እንዲኖረው ለማድረግ ቀደም ብሎ በበንሻንጉል ጉምዝ ምክርቤት የተዎሰነው ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ እንዲመች አሁን ለገላጋይ የሚያስቸግር ግጭት መፍጠር ስልታዊ የእቅድ አፈጻጸም መሆኑ።
3. ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ያልበለጠ ቋንቋ ተናጋሪ ያለው የቅማንት ማህበረሰብ የማንነት ጥያቄ በሚል ራሳቸውን በሾጡ የኮሚቴ አባላት በመመራት አማራ በድሎናል ከአማራ መለየት አለብን የሚል ታቅዶ የተፈተለ ገመድ ሞተሩ መቀሌ ላይ ሆኖ ህብረተሰብን ሰላም የመንሳት አጀንዳ የቅማንት ማንነት ሰሙ ሲሆን ወርቁ በምእራብ ጎንደር ቤንሻንጉል ከትግራይ ጋር እንዲዋሰን ማድረግና አስቀድሞ በቤንሻንጉል ምክርቤት የተወሰነው ውሳኔ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ነው።
4. የወልቃይት ጸገዴና የራእያ ማንነት ጥያቄዎች በተፋፋሙበት በአሁኑ ዎቅት ፈደሬሽን ምክር ቤት የማንነት ጥያቄ አልደረሰኝም በማለት በሊቀመንበሯ ኬሪያ ኢብራሂም በየጊዜው መግላጫ የሚሰጥበትና የትግራይ ክልላዊ መንግስትም በተደጋጋሚ በክልሉ የማንነት ጥያቄ የለም በማለት የሚክደው ዲሞግራፊውን የቀየረውን ውልቃይትን ሪፈረንደም እንዲደረግ ራያን ደግሞ የማንነት ጥያቄው ከገፋ ልዩ ዞን በማድረት ከአማራ ክልል ኦሮምያ ዞን ጋር በማዋኸድ የእነ ጃዋርን ካርታ ትግባራዊ ማድረግ መሆኑንና።
5. በመጨረሻም ከአማራ የጸዱ ሁለት ውይም ሶስት ሃገሮች መመስረት ግቡ የሆነ ግጭት ነው እየተከናዎነ ያለው።

ታዲያ ይህንን ታላቅ እቅድ የሚያውቁትና ታላቅ ትግራይን የሚጠብቁት የትግራይ ምሁራን፣ ፖለቲከኞችና ታዋቂ ሰዎች ወያኔን እንዲቃወሙ እንዴት መጠበቅ ይቻላል። አይኖቻቸው በህልም እንጀራ ታውረዋል ። በእርሻና በማእድን የበለጸጉትን ጋምቤላንና ቤንሻንጉልን በደቡብ ምስራቅ ደግሞ አፋርን በመያዝ አገር የመሆንን ህልም ያነገበው ወያኔን ከመደገፍ ሌላ ስበዊነትም ሆነ ፍት ሃዊነት

ውይም እኩልነት ሊታያቸው አይችልም።ተራው ህዝብም ቢሆን ምንም ኢትዮጵያን ወዳድና ደግ ቢሆን በገዛ ልጆቹ ላለፉት ሃያ ስምንት አመታት የተጋተውን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ከመቀበልና ተገፍቻለሁ በሚል ስነልቦና ከዚህ መሰሪ ቡድን ጋር ቢተባበር ሊፈርድበት የሚችል ማነው?የኦሮሞ ልሂቃን አሁን በመንቃት ላይ ናቸው። ቢሆንም ግን ታላቋን ኦሮሚያን መገንባት የሚለው የኦነግ ቀቢጸተስፋ ቅዠት በቀላሉ ከምሁራኑ ህሊና ሊዎጣ የሚችል አይደለም ። ላለፉት አመታት በሙሉ ይሰራ የነበረው የኦነግና የወያኔ እቅድ በተግባር ነበር። እሲኪ ከዚህ በታች የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ያዎጣውን ነውረኛ የካቲታል ፕሮጀት ኢንቨስትመንት አፈጻጸም እንመልከት።

**Table 7.3: Number and Capital of Operational Projects by Region**

| Regions | 2014/15 | | 2015/16 | |
|---|---|---|---|---|
| | No. of projects | Investment Capital | No. of projects | Investment Capital |
| Tigray | 49 | 207.3 | 45 | 111.5 |
| Afar | 15 | 97.5 | 6 | 16.0 |
| Amhara | 4 | 10.0 | 7 | 13.6 |
| Oromia | 304 | 1,398.4 | 26 | 345.9 |
| Somali | 0 | 0 | | |
| Benishangul-Gumuz | 0 | 0 | | |
| SNNPR | 1 | 13.8 | 2 | 5.2 |
| Gambella | 0 | 0 | | |
| Harari | 3 | 27 | | |
| Addis Ababa | 31 | 2,381.5 | 755 | 6,147.6 |
| Dire Dawa | 0 | 0 | 11 | 68.8 |
| Multiregional Projects | 0 | 0 | | |
| **Grand Total** | **407** | **4,135.0** | **852** | **6,708.6** |

Source: Ethiopian Investment Commission.

ህልም ሳይሆን እውን የሆነው ኢትዮጵያን የማፍረስ እቅድ ይሳካልናል ብለው ተፍተፍ በማለት የሚገኙት ህወሃትና ኦነግ አሁን የራስ ምታታቸው የኢትዮጵያ ህዝብ መንቃቱ ሳይሆን ዐማራ በተለየ መንገድ ሁኔታውን መገንዘቡ አብን የመሰሉ ንቅናቄዎች መመስረታቸውና ምእራባውያን ከመሸም ቢሆን መሰሪነታቸውን መረዳታቸው ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ድጋፍ መስጠታቸው ነው። ግማሽ ምእተ አመት የቆየውን ኦነግን በሽብርተኝነት የመዘገበችው አሜሪካ ለአብን ድጋፍ መስጠቷና ከተመሰረተ ወራት እንኳ ሳይቆይ ልኡክ

በመላክ ማነጋገሯ እንዲሁም አሁን ዶክተር አብይና ተከታዮቻቸው ኢትዮጵያን በተመለከተ እያራመዱት ያለውን አቋም መደገፋቸው ለአነግና ህወሃት ከፍታኛ መደናገጥን ፈጥሮባቸዋል።እ ኤ አ ዴሰምበር 12 ቀን 2018 ዓም በኔዘርላንድ ላይደን ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ ፋኩሊቲ የአፍሪካ ጥናት ምእከል ዴስክ የኢትዮጵያ ካንትሪ ሚቲንግ ፓናል አዘጋጅቶ በዚያ ተገኝቼ ነበር። በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያተኮሩ በፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጥናቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎ ነበር። በጥናታዊ ጽሁፎች እንደተገለጸውም 83 በመቶ የሆነው የሃገራችን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች እንደሆነ መስማት ምንኛ ያሳምማል። ፕሮፌሰር ያን አቢንክ ማለትም በዩኒቨርሲቲው የአፍሪካ ስተዲስ ማእከል ሃላፊ አገሪቱ ያለችበትን ተስፋና ስጋት በዝርዝር አቅርበዋል። የአብይ ተግዳሮቶች ብለውም የዘር ፖለቲካው የወለደውን ገሰኝነት ዋነኛው ችግር ብለው አቅርበውታል። በተለይም አሁን እያቆጠቆጠ ያለው የአማራ ብሄርተኝነት እጅግ አስጊ መሆኑንና ወያኔዎች እዚህም እዚያም እያነሱት የሉት ገጭት ለውጡን ወደ ኋላ እንዳይመልሰው እንደ ሚፈሩ ነገር ግን የእነ ዶክተር አብይ ቡድን ራሱን አዘጋጅቶ የቀረበ በመሆኑ በውስጡም በርካታ ለውጥ ደጋፊ ተከታዮች እንዳሏቸው ብዘው ስጋታቸውም በተስፋ የታጀበ መሆኑን አስረዱ። የዐማራ ብሄርተኝነት ለምን እንዳቆጠቆጠ ግን ለመናገር መክሬ ነበር። በዐማራ ላይ የተደረገው የዘር ማጥፋት ዘመቻ በዜዴ ከየክልሎችና ከመንግስት መስሪያቤቶች እንዲባረር መደረጉ ባጠቃላይ ህልውናውን ለማስከበር የጀመረው ሙከራ ነው። ዶክተር አብይ ለተፈጸሙ ስህተቶች ሁሉ መንግስታቸውን ወክለው የቅርታ ሲጠይቁ የአማራን ዘር መጠፋት በተመለከተ ግን ይቅርታ አልጠየቁም ። አሁንም ገና የዐማራው ጥያቄ ትኩረት አላገኘም በማለት አስተያየቴን ስወረውር ፕሮፌሰሩ  ዘር ማጥፋት የሚለው ቃል ይከብዳል የዘር ማጽዳት(ethnic cleaninsing) ቢባል የመጥናል በማለት በትክክል ይህንን እንደሚያውቁ በመላው ሃገሪቱ አማራ ከየቦታው እንዲፈናቀል መደረጉን አምነው አሁን ሃገሪቱ በልማትና በእርቅ ላይ ማተኮር እንዳለባት አሳሰቡ። የወያኔና የኦነግ ርዕዮተ አለም ግን በምእራባውያን ዘንድ ፈጸሞ የተናቀና የተጣለ መሆኑን በወቅቱ ተገንዝቤያለሁ።

## ማጠቃለያ

ለጊዜው የትግራይን ምሁራን ወይም የወያኔ ተቃዋሚ ነን ባዮች አጋራችን እንዲሆኑ የምናደርገውን ሙከራ ተወት አድርገን የተጠነሰሰውንና አገር የማፍረሱን ሴራ በጽናት መታገል የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ግዴታ ነው። ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ጋምቤላን ከቤንሻንጉል ቤንሻንጉልን ከትግራይ ለማዋሰን የሚደረጉ አዛኝ ቅቤ አንጓች እንቅስቃሴዎችን መግታት እንዲሁም የኦነግን ሳይበላው ማከክ አይነት ጉዞ ማስቆምና በሃሳብ ልእልና ህዝብን በአንድነት ማደራጀት የወቅቱ አንገብጋቢ ፖለቲካዊ አጀንዳ ማድረግ። የአብሮነትና የአንድነት እሴቶቻችንን ተቋማዊ ማድረግና ፍትህ እኩልነትና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን የዜግነት ግዴታችንን መወጣት አስፈላጊ ነው። ህልውናውን በማስጠበቅ አገርን ከመፍረስ  ሊታደግ የሚደራጀውን ዐማራ በማንኛውም መልኩ ድጋፍ እንጂ አፍራሽ አለመሆንም ወቅታዊ ግዴታችን ነው። ህወሃት **የትግራይ ህዝብ ጠላት እንጂ ነጻ አውጪ እንዳልሆነ የ**ትግራይ አክቲቪስቶች ያስገነዝባሉ ብሎ ማመን ግን ባለፉት አመታት እየተነገረን ያላመንነውን የታላቂቷ ትግራይን ምስረታ ተቃወሙ ማለት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

© በአዲስ ተስፋ

ዴሴምበር 2018